# ባርነትና ነብዩ መሀመድ

صَلَّى ٱللَّهُ عَلَيْهِ وَسَلَّمُ



ዐቅበተ ኢስላም ኑረዲን

የነቢዩ ሙሀመድን እውነተኛ ነቢይነት የማይቀበሉ ሚሽነሪዎችና ኦሬንታሊስቶች ከሚያነሷቸው ክሶች አንዱ"ነቢዩ ሙሀመድ በባሪያ ንግድ ውስጥ እጃቸው አለበትና የሰውን ልጅ እኩልነት አይቀበሉም።"የሚል ነው። የ"ትንቢተ-ነቢዩ ሙሀመድ፡ ንፅፅራዊ አቀራረብ"መፅሀፍ ፀሀፊ ርዕሰ ጉዳዩን እንደሚከተለው አብራርቶታል።

## ብኙታ ፮

## ባርነትና ነቢዩ ሙሀመድ (ﷺ)

በነቢዩ ሙሀመድ ﷺ ላይ ከሚቀርቡ ክሶች ሌላው "ነቢዩ ሙሀመድ ባሪያ በመግዛት፣ በመሸጥና ባሪያዎችን በማስተዳደር ላይ ስለተሳተፈ ባርነትን ደግፏል። ባርነትን አልተቃዎመም፤ ስለዚህ የሰዎችን እኩልነት አይቀበሉም።" የሚል ነው። በአብዛኛው ይህን ክስ የሚያሰሙት የውጭው ዓለም "ኤቲስቶችን" የሰሙ ምንም ዓይነት የክርስትና እውቀት የሌላቸው "ተቺዎች" ብቻ ናቸው። ምክንያቱም የባርነት ምንጩ መፅሀፍ ቅዱስ ነውና። መፅሀፍ ቅዱስ አንድም ቦታ ባርነትን ያልከለከለ ከመሆኑም ባሻገር ከዘፍጥረት እስከ ዮሐንስ ራዕይ ባርነትን ይደግፋል። የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚደንት ጀፈርሰን ደቪስ *"ባርነት በሀያሉ እግዚአብሔር ድንጋጌ የተመሰረተና ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ዮሐንስ ራዕይ ድረስ ባሉት ቅዱሳት መፃህፍት ውስጥ የተደገፈ ነው።"* ማለቱ ይነገራል። አሌክሳንደር ችምፕቤል የተባሉ ቄስም *"ባርነትን የሚከለክል የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ አንድም ቦታ አይገኝም። ስለዚህ ስብዕናን ይጋፋል ብለን አንደምድም።"* ብለዋል። ቄስ ሪቻርድ ፈርማን በበኩላቸው *"ባሮችን የማስተዳደር መብት በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ በተግባርም ሆነ ምሳሌያዊ በሆነ መልኩ በግልፅ የተቀመጠ መብት ነው።"* በማለት ባሪያን ማስተዳደር መፅሀፍ ቅዱሳዊ መብት መሆኑን ተናግረዋል። ይህንና መሰል አስተምህሮቶችን ያነበበ በባርነት ጉዳይ ነቢዩ ሙሀመድን የመውቀስ ሞራል አይኖረውም።

ነቢዩ ሙሀመድ ﷺ የእስልምናን ብርሃን ይዘው ብቅ ሲሉ የባሪያ አስተዳደር ዓለምን ወርሷት ነበር። የነቢዩ ﷺ ዘመን ዐረቦችም እንደቀሪው የዐለም ክፍል ባርነትን ተላብሰውት ነበር።

1, እንደ መድናና ጧኢፍ ያሉ ለምነት ያላቸው አካባቢዎች ለእርሻ ስራና ለእርባታ በርካታ ባሮችን ይፈልጋሉ።

2, ከእርሻ ስራ ውጭ ያሉት አካባቢዎች ደግሞ ለእርባታና ለንግድ ስራ የሚያግዙ ባሮች አሏቸው። መካና አካባቢዋ ደግሞ ከተለያየ ክፍል ለሀጅ የሚመጣን ማህበረሰብ ስለሚያስተናግዱ ከፍተኛ የንግድ እንቅስቃሴ ነበራቸው። ከሀጂ በተጨማሪ ከፍተኛ ንግድ የሚያካሂዱባቸውና የግጥም ውድድር የሚያደርጉባቸው ዑካዝ፣ መጀናህና ዙል-መጃህ የተባሉ ሶስት ገናና ፌስቲባሎች ነበሯቸው። በነዚህ ፌስቲባሎች ሁሉም የአረቢያ ጎሳዎች የሚመጡ ሲሆን በውድድሩ ያሸነፈው ግጥም በከዐባ ላይ የሚሰቀል ይሆናል። በመሆኑም የመካ ሰዎች ለንግድ ስራ ያግዟቸው ዘንድ በርካታ ባሮችን ያሰማሩ ነበር። ከውስጥ ንግድ በተጨማሪ በሲራራ ንግድ የተሰማራ ማህበረሰብ እንደመሆኑ ለወራት ጉዞ ወደ ሌሎች ሀገሮች ስለሚሄድ ራሱን በባሮች ጉልበት ላይ ያንጠለጠለ ማህበረሰብ ተፈጥሯል።

3, ዐረቦች በከፍተኛ ደረጃ የአልኮል ተጠቃሚ ስለነበሩ በርካታ ጨፋሪዎችና የአቀስት፣ የጦርና የሰይፍ ትርኢት የሚያሳዩ ባሮችም ነበሯቸው።

4, የጎሳ አስተዳደሮችና የተከበሩ ሰዎች በስራቸው በርካታ ባሮችንና ለሚስቶቻቸውም ጃንደረቦችን ይገዙ ነበር። አንዲት እመቤት ወደ ገበያ ለመሄድ ከ4 ያላነሱ ባሮችን ይዛ ትሄድ ነበር።

5, ዐረቦች ወደ ጦርነት ለመግባትና ደም ለመፋሰስ ያን ያክል በቂ ምክንያት ማግኘት የማስፈልጋቸው በጥቃቅን ምክንያቶች ጦርነት ውስጥ የሚገቡ ህዝቦች ነበሩ። በውኃ

ቀጠነ ብዙ ደም አፋሳሽ ጦርነትን ያደርጉ ነበር። ለምሳሌ፡- የበክር ጎሳ ግመል ከተግሊብ ጎሳ መሪ ግመሎች ጋር በርግጋ በመግባቷና በመገደሏ ምክንያት ተግሊቦችና በክርዮች ረጅም ጊዜ የፈጀ ጦርነት አድርገዋል። የግመሏን ካሳ በማስከፈል ብቻ ሰላም ማውረድ ሲቻል፤ የጦርነት ፍቅራቸው ብዙ ህዝብ ያለቀበት ረጅም ጦርነትን አስመርጧቸዋል። ይህ መፍቅረ ጦርነታቸውም የምርኮ ባሪያ የማግኘት እድላቸውን ጨምሮታል።

በአጠቃላይ በነቢዩ ሙሀመድ ﷺ ዘመን የኖረው ዐረብ ለምርኮ የሚዋጋ እስከቻለ ባሪያ ማርኮ ካልሆነም ከንብረት ምርኮ ተካፍሎ የመኖር ስነ-ልቦና ያለው ማህበረሰብ ነበር። "*የጎሳን ክብር ለማስጠበቅ ከሚደረጉ የብቀላ አዙሪቶች በተጨማሪ አንዳንድ የዐረብ ጎሳዎች ሌላውን ጎሳ በመውጋት በሚያገኙት ሃብትና ምርኮኞቻቸውን ለባርነት አዳልፎ በመስጠት በሚሰበስቡት ገንዘብ ይተዳደሩ ነበር።*" ይላል ዶር. ዐሊ ሙሀመድ አስ-ሶልላቢ የዐረቦችን የምርኮ ወዳድነት ሲገልፅ።[1]

## i, "ባርነት በቀጥታ ማውገዝና ባሮች ለነፃነታቸው እንዲፋለሙ ማድረግ"

ነቢዩ ﷺ የተላኩት ዐረቦች ከባሪያ ጋር በተያያዘ እጅግ ቁርኝት ፈጥረው በርካታ ባሮችን በሚያስተዳድሩበት ወቅት ነበር። የነቢዩ ﷺ የሰበካ ህይዎት በዋናነት የተላኩበትን ጉዳይ (የተውሒድ) ለማድረስ እጅግ ከባድ የነበረ ከመሆኑም ጋር"ጌታና ባሪያ እኩል ነው። ባሮች ሆይ አምፃችሁ ውጡ። ማንም የማንም ባሪያ አይሆንም።"ቢሉ ኖሮ ምን ሊከሰት ይችል ነበር? በእርጥ በዐረብ ያለው የባሪያ ቁጥርም የሚናቅ ስለማይሆን ብዙ ተከታይ ባሮችን ሊያገኙ እንደሚችሉ አያጠራጥርም። ሆኖም

ሀ, በ"ነፃ እወጣለሁ፤ አትወጣም"ሽርኩቻ ከባሮችም ከአሳዳሪዎችም በርካቶች ያልቃሉ፣ የንፁሀን ደም ይፈሳል፣ ህፃናትና ሴቶች ተጠቂ ይሆናሉ። በአጠቃላይ በሀገሪቱ ላይ ከፍተኛ የሆነ የደም ጎርፍ ያዳፋል። ይህ ደግሞ ከመሰረታዊ የእስልምና አስተምህሮት ጋር የሚጋጭ ነው።

[1] ለዓለማት እዝነት፡ (ትርጉም፡ አህመድ ሁሴን) ገፅ 51

ለ, ከፍተኛ ብር አውጥተው ባሮችን የገዙ የባሪያ አሳዳሪዎች ገንዘባቸውን ይከስራሉ። ነቢዩ ሙሀመድ ጥላቶቻቸውን እንኳን መጉዳት የሚፈልግ ስብዕና ያልነበራቸው ለሰው ሀቅ (ገንዘብ፣ ንብረት ወይም መብት) ተቆርቋሪና የማንም ሀቅ እንዳይጎድል ያስተማሩ ሰው በመሆናቸው ጠላቶቻቸውም ቢሆኑ እንኳን እንዲከስሩ አይፈልጉም።

ሐ, ለባሮች ምግብ፣ ልብስና መጠለያ የሚያዘጋጀው አሳዳሪያቸው ነው። ነገር ግን ባሪያው ሁሉ ከጌታው ከወጣ እነዚህን መሰረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት የሚያስችል አቅምን አያገኙም። ሙስሊሞች ደካማ በመሆናቸው በአንድ ጊዜ በርካታ ባሮችን ማኖር አይችሉም።

ስለዚህ ባርነት እጅግ የሚጠላ ተግባር ቢሆንም ባሮችን ማሳመፅ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናልና የዘመኑ "ሀያሲያን" ባይወዱላቸውም ውዱ ነቢይ ﷺ ይህንን መንገድ ፈፅመው አልተከተሉም። ከዚህ ይልቅ አንድ ሰው ባሪያ ሆኖ የሚፈነገልበትን ምክንያት በማጥበብ የባርነት መሰረቱን ነቀሉት።

– ሙስሊም በሙስሊም ባሪያ ሆኖ አይፈነገልም።

– አንድን ነፃ ሰው በጉልበት ባሪያ አድርጎ መፈንገልም አይቻልም።

– ነፃውን ሰው ባሪያ አስመስሎ መሸጥና ባሪያ ማድረግ አይቻልም። ቡኻሪ በዘገቡት ሀዲስ ነቢያችን *"በፍርድ ቀን እኔ ራሴ ከሳሽ የምሆንባቸው ሰዎች ሦስት ምድቦች አሉ፡ ከነዚህ ከሦስቱ አንዱ ነፃን ሰው ባሪያ አድርጎ ሸጦ ይህን ገንዘብ የበላ ነው።"*[2]

[2] ቡኻሪና ኢብኑ ማጀህ ዘግበውታል

ስለዚህ አንድ ሰው ባሪያ ሆኖ ሊፈነገል የሚችለው ሙስሊሞችን ሊዋጋ መጥቶ በጦርነቱ ላይ ከተማረከ ብቻ ነው። ውዱ ነቢይ ﷺ ከዚህ ውጭ ሙስሊሞች ማንንም ሰው በባርነት እንዳይፈነግሉ አሳሰቡ። ስለዚህ ሙስሊሞች ጦር መዞ፣ ቀስት ወድሮ ሊገላቸው የመጣና በለስ ያልቀናውን ተማራኪ ብቻ ባሪያ ያደርጉ ነበር። ጥበበኛው ነቢይ ﷺ ለጠላታቸውም እጅግ አዛኝ ነበሩና ለተማራኪ ባሪያውም እጅግ ዘርፈ ብዙ የነፃነት እድሎችን አመቻችተዋል።

## ii,"ጦርነትና ባርነት"

ሙስሊም በቁጥር እጅግ አናሳ በነበሩበት፣ ከሀዲያን ከያሉበት ተሰባስበው በአንድነት እስልምናና ሙስሊሞችን የተበተነ ትቢያ ሊያደርጓቸው ቋምጠው የመጡ ከሀዲያንን አስመልክቶ አምላካችን አላህ *"እነዚያንም የካዱትን (በጦር ላይ) ባገኛችሁ ጊዜ ጫንቃዎችን በኀይል ምቱ። ባደካማችኋቸውም ጊዜ (አትግደሏቸው ማርኳቸው)። ማሰሪያውንም አጥብቁ። በኋላም ወይም በነጻ ትለቋቸዋላችሁ፤ ወይም ትበዧቸዋላችሁ። (ይህም) ጦሪቱ መሳሪያዋን እስከምትጥል ድረስ ነው። (ነገሩ) ይህ ነው። አላህም ቢሻ ከእነርሱ (ያለጦር) በተበቀለ ነበር። ግን ከፊላችሁን በከፊሉ ሊሞክር (በዚህ አዘዛችሁ)። እነዚያንም በአላህ መንገድ ላይ የተገደሉትን ሥራዎቻቸውን ፈጽሞ አያጠፋባቸውም።"* [3] በማለት በጦርነት ወቅት ሙስሊሞች ምርከኞች ጦርነቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ አጥቀው እንዲይዙ ያዛል።[4] ጦርነቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ሙስሊሞች

---

[3] ሙሀመድ 47:4

[4] "ማሰሪያዎቻቸውን አጥብቁ" ማለት እንዳያመልጡ ወይም መሳሪያ ቀምተው ሙስሊሞችን እንዳይገድሉ ነቅታችሁ ጠብቁ ማለት ነው። ለምርከኞች ማዘንና ምርከኞችን መንከባከብ ደግሞ የሙስሊሞች መገለጫ ነው። ታላቁ ኢትዮጵያዊ ዓሊም ሸይኽ ኤሊያስ አህመድ "ይህ ነው የኛ ኢስላም" በሚለው ፅሁፉ *"ለምርኮኞች ማዘንና በጎ መዋል የጀነት ወራሾች መገለጫ ሆኖ ተወስቷል፦"ምግብንም ከመውደዳቸው ጋር ድሃን፣ የቲምንና ምርኮኛን ያበላሉ።"(አል-ኢንሳን 4፡8) ኢብኑ ዐብ-ባስ ይህን አንቀፅ አስመልክቶ እንዲህ ይላሉ፦"የዛኔ ምርኮኞቻቸው አጋሪያን ነበሩ።"(ተፍሲር ኢብኒ ከሢር፡ 8/288) ኢብኑ ከሢር አያይዘው እንዲህ ይላሉ፦"ለዚህ (ትርጓሜ) የሚመሰክረው መልዕክተኛው በበድር ዘመቻ ወቅት ምርኮኞችን እንዲንከባከቡ ሰሓቦቻችውን ማዘዛቸው ነው፤ እነርሱም በምግብ ወቅት ከራሳቸው ያስቀድሟቸው ነበር"አቡ ዑዘይር ኢብኑ ዑመይር ኢስላምን ሳይቀበል በፊት ስላጋጠመው ተያያዥ ጉዳይ እንዲህ ሲል ይመሰክራል፦"በበድር ጦርነት ከተማረኩት መካከል ነበርኩ፤ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ፦ "ለምርኮኞች መልካም የመዋልን አደራ ጠብቁ!" እኔም ከአንሷር ጭፍራዎች ጋር ነበርኩ፤ ቁርሳቸውንና እራታቸውን ባቀረቡ ጊዜ በመልዕክተኛው አደራ የተነሳ እነርሱ ቴምር በልተው እኔን ዳቦ ያበሉኝ ነበር"(አጥ-ጦበራኒ በሁለቱ መዕጀሞች ዘግበውታል፦ "መጅመዑ'ዝ-ዘዋኢድ" ቁጥር 10007 ይመልከቱ፤ በተጨማሪም "ሲረቱ ኢብኒ ሂሻም" (1/645) ይመልከቱ፡)"* በማለት የኢስላም የምርኮኛ አያያዝን አብራርቶ ፅፏታል።

ያለውን ነባራዊ ሁኔታና ጥቅምና ጉዳትን ካመዛዘኑ በኋላ ምርኮኞችን አስመልክቶ አራት ምርጫዎች ተሰጥቷቸዋል።

1, በነፃ መልቀቅ

2, ምርኮኛን በምርኮኛ መለዋወጥ፣ ካሳ (ቤዛ) ከፍሎ ነፃ የሚወጣም ካለ ነፃ እንዲወጣ ማድረግ

3, በልዩ ሁኔታ መገደል ያለባቸው ካሉ መግደል ለምሳሌ፦ ቀድሞ በነፃ ተለቆ በሌላ ጦርነት የተማረከ

4, ባሪያ አድርጎ መያዝ

ጥያቄ የሚነሳው በአራተኛው ምርጫ ነው። ሙስሊሞች ነባራዊ ሁኔታውን እንዲሁም ጥቅምና ጉዳትን አመዛዝነው ከምርከኞች በነፃ የሚለቁትን ለቀው፤ በቤዛ የወሰደውን ሰደው፤ በልዩ ምክንያት መገደል ያለበትን ወይም ከሀገር መሰደድ ያለበትን ከወሰኑ በኋላ የቀሩትን ባሪያ ያደርጋሉ። ምክንያቱም

**ሀ**, ለጦርነት ሊገድሉ ወይም ሊማርኩ የመጡ ጠላቶችን ማርኮ ነፃ መልቀቅ መልሶ እንዲወጋ ማበረታታት ነው። በለስ ባይቀናው እንጂ የመጣበት ዓላማ እስልምናን ሊያጠፋ፣ ነቢዩንና ባልደረቦቻቸውን ሊገድል፣ ባሪያ ሊፈነግል ነው። ስለዚህ ሊገድል የመጣን ምርኮኛ ነፃ አድርጎ መላክ አንገት ላይ ገመድ እንደማስገባት ይሆናል። በእድሜው የገፋ ወይም በሙስሊሞች ግምገማ በነፃ የሚለቀቁ እንዳሉ ሁሉ።

**ለ**, በነቢዩ ﷺ ዘመን አጥፊዎች የሚቀጡበት ማረሚያ ቤት አልነበረም። ነቢዩ አጥፊዎች ሲመጡ የሙስሊሞችን አምልኮና ሥነ-ምግባር ይማሩ ዘንድ መስጂድ ነበር የሚያስቀምጧቸው። የጦር ምርከኞችን ሁሉ መስጅድ ሰብስበው ቢያስገቡ እነርሱን መመገብ የሚያስችል አቅም አልነበራቸውም። ስለዚህ የግድ ምርከኞች በየሙስሊሙ ቤት በትኖ እየሰሩ እንዲበሉ ማድረግ ግድ ነው። እስልምናን ሊያጠፉ መጥተው ምርኮ የሆኑ በርካታ ባሮች የሙስሊሞችን አምልኮና ሥነ-ምግባር ሲያዩ እስልምናን እንዲወዱ አድርጓቸው ሰልመዋል።

**ሐ**, አንድ የቀረ ምርጫ ግን አለ። በለስ ባይቀናው እንጂ እስልምናን ሊያጠፋ፣ ነቢዩንና ሙስሊሞችን ሊገድ የመጣን ሰው ነፃ መልቀቅ የማይቻል ከሆነና ባሪያ ሆኖ አሳዳሪው ከሚበላው በልቶ፣ እንደ አሳዳሪው ለብሶ መኖር ኢ-አመክኗይ ነው ካልን ሶስተኛው ምርጫ ምርኮኛ ነውና አሰቃይቶ መረጃ አስወጥቶ መግደል ተገቢና አመክኗዊ ተግባር ነው። (የዘመናችንን የምርኮኛ አያያዝ ከነብዩ አስተምህሮት ጋር አነፃፅሩት) ሊገድል መጣ፣ ካልገደለ መገደሉ እጣ ፈንታው ነው።"ከመሞት መሰንበት"ነውና ኢስላም ባርነታቸውን መርጧል።

ይህ ምርኮኛን ከመግደል ይልቅ ባሪያ ማድረግና ነፃነቱን ተስፋ እንዲያደርግ ማበረታታት ምን ያክል ከፍ ያለ መለኮታዊ ተግባር እንደሆነ ለመገንዘብ የተወሰኑ የመፅሀፍ ቅዱስ ታሪኮችን ማየት እጅግ አስፈላጊ ነው።

"ያንዳንዷ ቆንጆ ሴት ውበት የሚጎላው፣

በምታስከትላት አስጠሊታ ሴት ነው።"[5]

እንዲል ገጣሚው የአንዳንድ እውነቶች ውበት በፈቃራኒያቸው እጅግ ይጎላል። የተውሒድን ብርሃን ለመገንዘብ፤ የሽርክን ጨለማነት ማወቅ ያስፈልጋል። አብዛኛው የነቢዩ ሙሀመድ ﷺ አስተምህሮቶችም የሌላ እምነት"መለኮታዊ"መፅሀፍቶችን ካላጠኑ ግልፅነቱ፣ ብርሃናማነቱ፣ ሜዳማነቱና ጥርት ያለ መሆኑ ግልፅ ላይሆን ይችላል። እዚህም እንዲሁ ነው። በመፅሀፍ ቅዱስ የጦር ምርኮኛ ሆኖ ባሪያ መሆን ከመቶ አንድ ጊዜ ብቻ ሊገኝ የሚችል እድል ነው። ይሄውና ምሳሌዎቹ

**1**,"የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እስራኤል ከግብፅ በወጣ ጊዜ አማሌቅ በመንገድ እየተቃወመ ያደረገበትን እበቀላለሁ። አሁንም ሄደህ አማሌቅን ምታ፣ ያላቸውንም ሁሉ ፈጽመህ አጥፋ፣ አትማራቸውም፤ ወንዱንና ሴቱን ብላቴናውንና ህጻኑን

[5] ይስማዕከ ወርቁ፡ የቀንድ አውጣ ኑሮ፡ ገፅ 58

በሬውንና በጉን ግመሉንና አህያውን ግደል።" ዝቅ ብሎም "የአማሌቅንም ንጉስ አጋግን በሕይወቱ ማረከው፥ ሕዝቡንም ሁሉ በሰይፍ ስለት ፈጽሞ አጠፋቸው።" [6] በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ነው እንግዲህ ይህ ሁሉ ጥፋት። አንድ እንኳን በምርኮ የቀረ የለም። ሁሉንም ነው እንዳለ እንዲጠፉ ያዘዘው። በጦርነት መካከል "*ከአጋሪዎችም አንዱ ጥገኝነትን ቢጠይቅ የአላህን ቃል ይሰማ ዘንድ አስጠጋው። ከዚያም ወደ መጠበቂያው ስፍራ አድርሰው። ይህ እነሱ የማያውቁ ሕዝቦች በመኾናቸው ነው።*" [7] የሚለው የአምላካችን ቃል ምንኛ ያማረ ነው!

2,"እግዚአብሔርም፦ ሴዎንንና ምድሩን በእጅህ አሳልፌ መስጠት፥ እነሆ ጀመርሁ፤ ምድሩን ትገዛት ዘንድ መውረስ ጀምር፤ አለኝ። ሴዎንም ሕዝቡም ሁሉ ሊጋጠሙን ወደ ያሀጽ ወጡ። አምላካችንም እግዚአብሔር እርሱን አሳልፎ ሰጠን፤ እርሱንም ልጆቹንም ሕዝቡንም ሁሉ መታን። በዚያን ጊዜም ከተሞቹን ሁሉ ወሰድን የተቀመጡባቸውንም ሰዎች ሁሉ ሴቶችንም ሕፃናቶችንም አጠፋን፤ አንዳችም አላስቀረንም!"[8]

3,"ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር ርስት አድርጎ ከሚሰጥህ ከእነዚህ አሕዛብ ከተሞች ምንም ነፍስ አታድንም። ነገር ግን ለአማልክቶቻቸው ያደረጉትን ርኵሰት ሁሉ ታደርጉ ዘንድ እንዳያስተምሩአችሁ፥ በአምላካችሁም በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት እንዳትሠሩ፥ አምላክህ እግዚአብሔር እንዳዘዘህ ኬጢያዊውን አሞራዊውንም ከነዓናዊውንም ፌርዛዊውንም ኤዊያዊውንም ኢያቡሳዊውንም ፈጽመህ ታጠፋቸዋለህ።"[9]

4,"በከተማይቱም የነበሩትን ሁሉ፥ ወንዱንና ሴቱን፥ ሕፃኑንና ሽማግሌውን፥ በሬውንም በጉንም አህያውንም፥ በሰይፍ ስለት ፈጽመው አጠፉ።"[10]

[6] መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 15:2-3፣ 8

[7] አት-ተውባ 9:6

[8] ኦሪት ዘዳግም 2:31-34

[9] ኦሪት ዘዳግም 20: 16-18

[10] መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ 6:21

5,"እግዚአብሔርም፦ በከተማይቱ በኢየሩሳሌም መካከል እለፍ፥ በመካከልዋም ስለ ተሠራው ርኵሰት ሁሉ በሚያለቅሱና በሚተክዙ ሰዎች ግምባር ላይ ምልክት ጻፍ አለው። እኔም እየሰማሁ ለሌሎቹ። እርሱን ተከትላችሁ በከተማይቱ መካከል እለፉ ግደሉም፤ ዓይናችሁ አይራራ አትዘኑም፤ ሽማግሌውንና ጐበዙን ቈንጆይቱንም ሕፃናቶቹንና ሴቶቹን ፈጽማችሁ ግደሉ፤ ነገር ግን ምልክቱ ወዳለበት ሰው ሁሉ አትቅረቡ፤ በመቅደሴም ጀምሩ አላቸው። በቤቱም አንጻር ባሉ ሽማግሌዎች ጀመሩ። እርሱም፦ ቤቱን አርክሱ፥ በተገደሉትም ሰዎች አደባባዮችን ሙሉ፤ ውጡ አላቸው። እነርሱም ወጥተው በከተማይቱ ገደሉ።"[11]

"በአላህ ስም፣ በአላህ ታግዛችሁ በመልዕክተኛው መንገድ ላይ ጉዞ ጀምሩ፤ ያረጀ ሽማግሌን፣ ህፃንን፣ (ያልደረሰ) ልጅንና ሴትን አትግደሉ! .."[12] የሚለው የመልዕክተኛው ንግግር ብቻ መለኮታዊነታቸውን ያሳይ ነበር ማስተዋል ለሚችል።

6,"የእስራኤልንም አምላክ እግዚአብሔርን የማይፈልግ ታናሽ ወይም ታላቅ፣ ወንድ ወይም ሴት ቢሆን ይገደል ዘንድ ማሉ።"[13]

7,"አንቺ ወራዳ የባቢሎን ልጅ ሆይ! ስለተበቀልሽን የሚበቀልሽ የተመሰገነ ነው። ሕፃናቶችሽን ይዞ በአለት ላይ የሚፈጠፍጣቸው የተመሰገነ ነው።"[14]

"*ሁሉንም ነገር መርምሩ፤ መልካም የሆነውን አጥብቃችሁ ያዙ።*"[15] እንዳለው ጳውሎስ መልካሙን የመምረጥ ስራ የአንባቢ ነው። መፅሀፍ ቅዱስ ምርከኞች ለምስክርነት አንድ

[11] ትንቢተ ሕዝቅኤል 9:4-7

[12] አቡ ዳዉድ - ቁጥር (2614)

[13] መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 15:13

[14] መዝሙር ዳዊት 137:8-9

[15] 1 ተሰሎንቄ 5:21 (የአድስ ዐለም ትርጉም)

እንኳን ሳይቀር በተመዘዘ ሰይፍ እንዲቀሉ፤ በተወደረ ፍላፃ እንዲጨፈጨፉም ያዛል። እስልምና ግን በተቃራኒው ምርከኞች በእንክብካቤ ተይዘው የሚለቀቁት ተለቀው፣ የቀሩት ጌታቸው ከሚበላው ሊበሉ፣ ከሚለብሰው ሊለብሱ መለኮታዊ ትዕዛዝ ወርዶላቸው ይፈነገላሉ። በሙስሊሞች ስር ያለ ምርኮኛ ታሪክ ባሪያ በመሆኑ ብቻ አይደመደምም። በተቃራኒ "*ከመኖር ተስፋ አለ፡ ከመሞት ምን ሊገኝ*" እንደተባለው እስልምና ለባሮች እጅግ በርካታ የነፃነት ተስፋዎችን ሰጥቷል። ከአንባቢ የሚጠበቀው የጳውሎስን ምክር እያሰላሰሉ ማንበብ ብቻ ነው።

## iii, ነቢዩ ﷺ ባርነትን በምን መልኩ ተቃወሙ?

ባርነት እጅግ የሚወገዝ ተግባር በመሆኑ ላይ ሁሉም ይስማማል። እስልምና ከማውገዝም አልፎ ምንጩን አድርቆታል፤ የቀረው ባሮችን ነፃ አድርጎ ማሰናበት ብቻ ነው። ከላይ እንዳየነው በእስልምና ነፃ የሆነን ሰው ባሪያ አድርጎ መሸጥ ክልክል ነው፣ ሙስሊምን ባሪያ ማድረግ ክልክል ነው። እስልምናንና ሙስሊሞችን ለማጥፋት በጂሀድ ላይ የተያዘ ምርኮኛ ብቻ ነው ባሪያ ተደርጎ የሚያዘው። ባሪያ ሆኖ ሲፈነገል በሙስሊሞች ስር በመሆኑ ብቻ ከሚያገኛቸው በርካታ እድሎች በተጨምሪ ነፃ የሚወጣባቸውን መንገዶች ሁሉ እስልምና አመላክቶታል። እስልምና የባሪያን ነፃነት እንደት በአንክሮት እንዳየው የምንገነዘበው በሀዲስ ሰብሳቢዎች ዘንድና በፊቅህ ኪታቦቻችን ውስጥ"ኪታቡል ኢትቅ"እንዳለ ስንገነዘብ ነው።

### 1, እኩልነትን መስበክ

ኢስላም የሰው ልጅ በአጠቃላይ እኩል እንደሆኑና የትኛውም ወገን ከየትኛው እንደማይበልጥ አስተምሯል። አምላካችን አላህ "*እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና*

*ከሴት ፈጠርናችሁ። እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ። አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው። አላህ ግልጽን ዐዋቂ ውስጥንም ዐዋቂ ነው።*"[16] በማለት ሰዎች አላህን በመፍራት ብቻ እንጂ በዘር፣ በጎሳ፣ በነገድና በሌላ በምንም እንደማይለያዩ ይነግረናል። ይህ አስተምህሮት ሰዎች በተፈጥሯቸው ነፃ እንደሆኑና የሆነን ነገድ ወይም የቆዳ ቀለም ያላቸውን ህዝቦች ባሪያ ማድረግ እንደማይቻል ያስገነዝባል። የክርስትና ሀይማኖት ባርነትን የጀመረውና እስከ 20ኛው መቶ ክፍለ ዘመንም ይዞት የቆየው የቆዳ ቀለምን መሰረት አድርጎ "ያንን የቆዳ ቀለም ባሪያ አድርጎ የመግዛት መለኮታዊ ስልጣን ተሰጥቶናል"በሚሉ የክርስትና"ሊቃውንት"መሪነት ነው። እስልምና ለባሪያዎች ዘብ ለመቆም ከታተረባቸው ጉዳዮች ዋናው ይህንን እሳቤ መበጣጠሱ ነው። እስልምና ነጩ ከጥቁሩ፣ ዐረቡ ከሌላው እንደማይበልጥ ያስተማረ ብቸኛው ሀይማኖት ነው። በዚህ የእስልምና አስተምሮ የባርነት መሰረቱ ድባቅ ተመቷል።

## 2, ለባሮች መልካም መዋልን ማስተማር

ውዱ ነቢይ ሙሀመድ ﷺ "*እነርሱ (አገልጋዮቻችሁ) አላህ በእናንተ ስር እንዲኖሩ ያደረጋቸው ወንድሞቻችሁ ናቸው። ከምትበሉት አብሏቸው፣ ከምትለብሱትም አልብሷቸው፤ የማይችሉትን እንዲሰሩ አትዘዟቸው፣ ካሰራችኋቸው ደግሞ አግዟቸው።*"[17] በማለት የባሪያ አሳዳሪዎች ለባሮቻቸው እንዲያዝኑ፣ ከባባድ ስራን እንዲያግዟቸው፣ ከአቅማቸው በላይ እንዳያዟቸው፣ ከሚበሉት እንዲያበሏቸውና እንዲያለብሷቸው አስተምረዋል። በዚህ አስተምህሮታቸው ባሮች በባርነት ውስጥም ሆነው የተሻለ እንዲኖሩ አስችሏቸዋል። አንድ ሊገድል ወይም ሊማርክ የመጣ "ጦረኛ" በባርነት ውስጥ ይህንን የመሰለ እንክብካቤ እንዲያገኝ ማስቻል ከየትኛውም ፍትሐዊ ሰው የሚጠበቅ አይደለም። ሆኖም ነቢዩ ሙሀመድ ﷺ መለኮታዊ ነቢይ ናቸውና አደረጉት። ሊገድላቸው ለመጣና በለስ ላልቀናው ሰው ደህንነትና እንክብካቤ እንዲደረግለት አዘዙ።

[16] ሁጅራት 49:13

[17] ቡኻሪ ዘግበውታል

## 3, ባሮችን ነፃ የሚወጡበትን ሁኔታ ማመቻቸት

ምንም እንኳን ባሪያ የሆነበት ምክንያት ከስለት የቀደደ፤ ከተራራ የከበደ ቢሆንም እስልምና ባሮች ነፃ ሊወጡበት የሚችሉ በርካታ መንገዶችን ያመቻቸው ብቸኛ ሀይማኖት ነው።

ሀ, ባሮች ራሳቸውን ነፃ የሚወጡበትን መንገድ ማመቻቸት፡- ባሮች በራሳቸው ጥረት ወይም በልዩ ምክንያት ራሳቸውን ነፃ የሚያወጡበት መንገድ ተመቻችቶላቸዋል። እነዚህም

**ሙካተብ**፡- ባሮች ራሳቸውን ለመግዛት ከአሳዳሪያቸው ጋር ስምምነት መፍጠር ይችላሉ። አምላካችን አላህ በተከበረ ቃሉ "*እነዚያንም እጆቻችሁ ከጨበጧቸው አገልጋዮች (ገንዘብ ሰጥተው ነጻ ለመውጣት) መጻጻፍን የሚፈልጉትን ከእነሱ መልካምን ነገር ብታውቁ ተጻጻፉዋቸው። ከአላህም ገንዘብ ከዚያ ከሰጣችሁ ስጧቸው።*"[18] በማለት ትልቁ የነፃነት ምንጭ አብስሯቸዋል። (ያን ቀን ባሮች እንደት ይደሰቱ! አጂብ) ለዚህም ሰዓት አመቻችተው የግል ስራዎችን ይሰራሉ፣ ሰርተው ገንዘቡ ካልበቃቸው አላህ በርካታ መንገዶችን አመቻቶላቸው።

1, ከዘካ ገንዘብ ይሰጣቸዋል፡- አምላካችን አላህ ዘካ የሚሰጣቸውን ሰዎች ሲዘረዝር "*ግዴታ ምጽዋቶች (የሚከፈሉት) ለድኾች፣ ለምስኪኖችም፣ በርሷም ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች፣ ልቦቻቸውም (በእስልምና) ለሚለማመዱት፣ ጫንቃዎችንም (በባርነት ተገዢዎችን) ነጻ በማውጣት፣ በባለ ዕዳዎችም፣ በአላህ መንገድም በሚሠሩ፣ በመንገደኛም ብቻ ነው። ከአላህ የተደነገገች ግዴታ ናት። አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው።*"[19] በማለት ራሱን ነፃ ለማውጣት ለተስማማ ባሪያ የዘካ ገንዘብ

[18] አን-ኑር 24፡33

[19] አት-ተውባ 9፡60

እንዲሰጠው ግደታ አድርጓል። ሀሰኑል በስሪይ፣ ዑመር ኢብን አብዱል አዚዝ፣ ሰኢድ ኢብኑ ጁበይርና ሌሎችም በዚህ አንቀፅ ሪቃብ በሚለው የተፈለጉት *"ለአሳዳሪያቸው የተወሰነ ቤዛ ከፍለው ነፃነታቸውን ለማግኘት የተስማሙ ባሮች ናቸው።"* ማለታቸውን ኢብኑ ከሲር በተፍሲሩ ገልፀአል።

**2**, አሳዳሪው ራሱ ገንዘብ እንዲሰጠው፡- ከላይ ባለው አንቀፅ ላይ እንደተቀመጠው የባሪያ አሳዳሪው መፃፃፍ ብቻ ሳይሆን ገንዘብም እንዲሰጠው"*ከአላህም ገንዘብ ከዚያ ከሰጣችሁ ስጧቸው።*"በማለትም አነሳስታል።

**3**, ሌላው ሙስሊም፡- አምላካችን አላህ ስለ መልካም ስራ ሢያወሳ "*ለጫንቃዎችም (ማስለቀቅ) የሰጠ*" ብሏል። [20] ኢብኑ ከሲር ይህን አንቀፅ ሲያብራራ *"እነዚህ አገልጋዮች ራሳቸውን ነፃ ለማውጣት የሚሹ፣ ነገር ግን ነፃነታቸውን ለመግዛት የሚያስችል በቂ ገንዘብ ያላገኙ ናቸው።"* ብሏል። ይህ ማለት ከአሳዳሪው ጋር ለተፃፃፈ ሰው ገንዘብ መስጠትና ነፃነቱን እንዲያገኝ ማገዝ ከመልካም ስራዎች ነው። ተፃፃፊው ባሪያም ሙስሊሞችን በማናገር ነፃነቱን መጎናፀፍ ይችላል።

**ሙደበር**፡- እነዚህ ደግሞ አሳዳሪያቸው ሲሞት ነፃ ሊሆኑ ቃል የተገባላቸው ናቸው።

**ኡሙል ወለድ**፡- ከአሳዳሪዋ የወለደች ባሪያ ኡሙል ወለድ ስትባል አሳዳሪዋ ሲሞት ነፃ ትሆናለች።

## ለ, አሳዳሪዎች ባሪያን ነፃ እንዲያደርጉ ግደታ መጣል

እስልምና ባሮች ራሳቸውን ነፃ እንዲያወጡ ከማበረታታት ባለፈ አሳዳሪዎች ባሪያቸውን ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ ነፃ እንዲያደርጉ ግደታም አድርጓል። ለዚህ የተከተለው ሰዎች

[20] አል በቀራህ 2:177

ለሚያጥውፏቸው ሸሪዓዊ ጥፋቶች ማሰሪያ ይሆን ዘንድ ባሮችን ነፃ እንዲያወጡ በማድረግ ነው። በኢስላም የበርካታ ሸሪዐዊ ጥፋቶች ማሰሪያው ባሪያን ነፃ ማድረግ ሲሆን ባሪያ ከሌለው ብቻ ነው አጥፊው ወደሚችለው የወንጀል ማሰሪያ መንገዶች ዝቅ የሚለው። ለምሳሌ

**በስሕተት ሰውን የገደለ**፡- *"ለምእመንም በስሕተት ካልኾነ በቀር ምእመንን መግደል አይገባውም። ምእመንንም በስህተት የገደለ ሰው ያመነችን ጫንቃ (ባሪያ) ነጻ ማውጣትና ወደ ቤተሰቦቹም የምትሰጥ ጉማ ምሕረት ካላደረጉለት በስተቀር (መክፈል) አለበት። እርሱ (ተገዳዩ) ምእመን ሲኾን ለእናንተ ጠላት ከኾኑትም ሕዝቦች ቢኾን ያመነችን ጫንቃ ነጻ ማውጣት (ብቻ) አለበት። በእናንተና በእነሱ መካከል ቃል ኪዳን ካላቸውም ሕዝቦች ቢኾን ወደ ቤተሰቦቹ በእጅ የምትሰጥ ጉማና ያመነችን ጫንቃ ነጻ ማውጣት አለበት። ያላገኘ ሰውም ተከታታዮችን ሁለት ወሮች መጾም አለበት። አላህ መጸጸትን ለመቀበል (ደነገገላችሁ)። አላህም ዐዋቂ ጥበበኛ ነው።"*[21]

**መሀላ**፡- ማንኛውም መሀላ ሳይሆን *"ታስቦበት የሚወጣ የመሀላ አይነት ነው።"ወላሂ ይህን ላደርግ፣ ወይም ላላደርግ"በሚል መልኩ፣ ባለፈ ሳይሆን ወደ ፊት ባለ ነገር ላይ፣ በማይታሰብ ሳይሆን መሆን በሚችል ጉዳይ ላይ ታስቦ የወጣ መሀላ ሲሆን ሰውየው መሀላውን ካልጠበቀ ማካካሻ (ከፋራ) ይጠብቀዋል።"*[22] አምላካችን አላህ ስለ ማካካሻው ሲያብራራ *"አላህ በመሐላዎቻችሁ በውድቁ አይዛችሁም። ግን መሐላዎችን (ባሰባችሁት) ይይዛችኋል። ማስተሰሪያውም*

[21] አን-ኒሳእ 4:92

[22] መሀላን የሚመለከቱ ሸሪዓዊ ህጎች፡ ኢብኑ ሙነወር፡ ሚያዚያ 1/2010 በማህበራዊ ሚዲያ የተፃፈ

*ቤተሰቦቻችሁን ከምትመግቡት ከመካከለኛው (ምግብ) ዐስርን ምስኪኖች ማብላት ወይም እነሱን ማልበስ ወይም ጫንቃን ነጻ ማውጣት ነው፤ (ከተባሉት አንዱን) ያላገኘም ሰው ሦስት ቀኖችን መጾም ነው፤ ይህ በማላችሁ ጊዜ የመሐላዎቻችሁ ማካካሻ ነው። መሐላዎቻችሁንም ጠብቁ። እንደዚሁ አላህ ለናንተ አንቀጾችን ያብራራል። እናንተ ልታመሰግኑ ይከጀላልና።*"[23]

– "*እነዚያም ከሚስቶቻቸው እንደናቶቻችን ጀርባዎች ኹኑብን በማለት የሚምሉ ከዚያም ወደ ተናገሩት የሚመለሱ ሳይነካኩ በፊት ጫንቃን ነጻ ማውጣት በነርሱ ላይ አለባቸው። እነሆ በእርሱ ትገሰጹበታለችሁ። አላህም በምትሠሩት ሁሉ ውስጥ ዓዋቂ ነው።*"[24] ባሪያ ነፃ ሳያደርጉ በፊት ፆታዊ ግንኙነት ማድረግ አይችሉም።[25]

**ፆሙን በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ያበላሸ**፡- ያንን ቀን መክፈል፣ እንዲሁም ለሠራው ወንጀል ማበሻ፣ ባሪያን ነፃ ማውጣት አለበት። ይህም፣ ሙስሊም ባሪያን በመግዛትና ከባርነት ቀንበር በማላቀቅ ይተገበራል። ባሪያን ነፃ ማውጣት የማይቻል ከሆነ፤ ሁለት ወሮችን በተከታታይ ይጾማል፤ ይህንንም ካልቻለ ስልሳ ሚስኪኖችን ያበላል።

## 4, አሳዳሪዎች ባሪያ ነፃ እንዲያወጡ ማነሳሳት

ኢስላም ባሪያን ነፃ በማውጣት ላይ አነሳስቷል። ባሪያ ነፃ ማውጣት ትልቅ ደረጃ እንዳለውም ነቢዩ አስተምረዋል አስተምረዋል። ባሪያን ነፃ በማድረግ ከተሰጡ በርካታ ትምህርቶች አንድ ሁለቱን ልጥቀስ

[23] አል ማኢዳህ 5:89

[24] አል ሙጃደላ 58:3

[25] ሱነን አን-ነሳኢ 3457

– አቡ ሀረይራ ባስተላለፈው ሀዲስ ነቢዩ ﷺ እንዲህ ብለዋል "*ሙስሊም የሆነን ባሪያ ነፃ ያወጣ (ነፃ ባወጣው ባሪያ) የሰውነት ክፍል በተመሳሳይ አካሉን ከገሀነም እሳት ነፃ ያወጣለታል። ብልቱ በብልቱ ሳይቀር።*"[26]

– አቡ ኡማማ በዘገበው ሀዲስ ነብዩ ሙሀመድ ﷺ እንዲህ ብለዋል "*ማንኛውም ሁለት ሴት ባሮችን ነፃ ያወጣ፤ ከእሳት መውጫው ይሆኑታል።*"[27]

በዚህ አስተምህሮታቸው ምክንያት እጅግ በርካታ ባሮች ነፃ ከመውጣታቸውም ባሻገር የነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ባሪያዎችን ነፃ ለማውጣት ይወዳደሩ ነበር። ነብዩ ﷺ በግላቸው 77 ባሪያዎችን ነፃ አውጥተዋል። በባለቤታቸው ዓኢሻ የተፈቱት ባሮች ቁጥር 69፣ አጎታቸው አባስ 70 ባሮችን ለቋል። ኡስማን ኢብኑ አፋን 20 ባሮችን ነፃ ያደረገ ሲሆን ሀኪም ኢብኑ ሂዛም 100 ባሮችን ነፃ አድርጓል። የሁለተኛው ኸሊፋ ልጅ አብደላህ ኢብኑ ዑመር አንድ ሺህ ባሮችን ነፃ አውጥቷል፣ ሌላው ባልደረባቸው አብዱረህማን ደግሞ 30,000 ባሮችን ገዝቶ ነፃ አወጣቸው። ዙልኺላ አል-ሒሚያሪ የተባለ ሱሀባም 8000 ባሮች በአንድ ቀን ነፃ እንዳወጣ ይነገራል። ይህ ሁሉ የነቢዩ ሙሀመድ ባሪያን ነፃ በማድረግ ላይ የማነሳሳታቸው ውጤት ነው።[28]

## 5, ባሮች ነፃ ከወጡ በኋላ በኢኮኖሚ እንዳይቸገሩ ማድረግ

ነቢዩ ﷺ ሂደታዊ የሆነን የባሪያ ነፃነት በመከተላቸው ነፃ የወጡ ባሮች እንዳይቸገሩ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። ከዚህ በተጨማሪም ነቢዩ የተለያዩ ዘደዎችን በመጠቀም ነፃ የወጡ ባሮች በኢኮኖሚው ዘርፍ እንዳይጎዱ አድርገዋል። ከነዚህ መንገዶች ጥቂቶቹ

**፩, ዊሊያ (ወዳጅነት፣ ጓደኝነት)**፦ ነቢዩ ﷺ በሀድሳቸው"ዊሊያ ነፃ ላወጣ ነው"በማለት ነፃ የወጣውና ነፃ አውጪው ወዳጆች እንደሆኑ፣ ባሪያው ቢሞት ወዳጁ ወራሹ እንደሆነ፣

[26] ሙስሊም 1509

[27] ቲርሚዚ፡ 1419

[28] https://www.islamiqate.com/3938/how-many-slaves-did-the-companions-sahaba-free

ነፃ አውጪውም ያለ ወራሽ ቢሞት መውላው ወራሽ እንደሆነ ተናገሩ። በዚህ በነፃ አውጪና በባሪያው መካከል ጥሩ ወዳጅነትን ፈጠርሩ። ይህ ጓደኝነት ለመረዳዳት፣ ለመተጋገዝና አብሮ ለመስራት ትልቅ እገዛ አድርጓል።

**፪, ዘካ**፡- ነቢዩ ﷺ ችግርተኞችን ለማገዝ የተከተሉት ትልቁ ኢኮኖሚያዊ መንገድ ተመጣጣኝ የዘካ ግደታ ነው። ዘካ ነፃ የወጡ ባሮችን ጨምሮ በርካታ ዘካ የተፈቀደላቸው ሰዎች አቅም እስኪያገኙ የሚደጎሙበት ትልቁ መንገድ ሆነ። ሸይኽ ኤሊያስ አህመድ የዘካን ድንጋጌ ጥበቦች ሲያሰፍር *"የዘካ ድንጋጌ እንደ ሌሎች መለኮታዊ ህግጋት ከአምልኮ ዘርፍነቱ ባሻገር ድንቅ፣ ብርቅና ጽድቅ ጥበቦችንና አላማዎችን ያነገበ ነው። ሰዎች ሊረዷቸው ከሚችሏቸው ግለሰባዊና ማህበራዊ ጥቅሞቹና የመፍትሄነት ገፅታዎቹ መካከል፡-*

*1. ለችግረኞች መረጃ መሆኑ፣*

*2. ለድሆች መቋቋሚያ መሆኑ፣*

*3. በእምነት ላይ የተመሠረተ የወዳጅነትና የወንድማማችነት ትስስርን ማጥበቁ፣*

*4. ስብዕናን ከስስትና ከንፈግነት ማፅዳቱ፣*

*5. ድሆች ለሀብታሞች ያላቸውን ምልከታ ከምቀኝነት ማጥራቱ፣*

*6. በድህነት ምክንያት የሚፈጸሙ ወንጀሎችን መገደቡ፣*

*7. ከገንዘብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥቅል ኢስላማዊ ጉዳዮችን ለማቀላጠፍ ምክንያት መሆኑና*

*8. የንብረት በረከት ማስከተሉ ጥቂቶቹ ናቸው።"* ሲል ፅፏል።[29] እነዚህ የዘካ ግለሰባዊና ማህበራዊ ጠቀሜታዎች ነፃ ለሆነ ባሪያ ይበልጥ ተገቢነት ያላቸው መሆኑን ልብ ይበሉ።

[29] የዘካ ህግጋት አጭር ማብራሪያ፡ ሸይኽ ኤሊያስ አህመድ፡ ገፅ 1-2

**፫, የንግድ ሥርዓትና ህግጋትን ማስተማር**፡- በእስልምና የሸሪዓ አስተምህሮ ከፍተኛ ትኩረት ከተሰጣቸው አንዱ ንግድ ነው። ነቢዩ ﷺ የንግድ ሥርዓትንና ህግጋትን አዘውትረው ማስተማራቸው፤ ነፃ የወጡ ባሮች በውክልናም ይሁን በሸርካ አብረው እንዲሰሩና በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉ ቦታን ከፍቷል።

**ማጠቃለያ**፡- ነቢዩ ሙሀመድ ﷺ እና ሙስሊሞች የተሳተፉት ነፃ ሰዎችን ባሪያ ማድረግ ላይ ሳይሆን፤ ባሮችን ነፃ ማድረግ ላይ ነበር። የዓለም ህዝብ ሁሉ ባሪያ አሳዳሪ በሆነበትና ባሪያን መፈንገል እንደ ጀብድ በሚታየበት ዘመን ተከስቶ ባሮችን ነፃ ለማድረግ ብቻ በባሪያ ንግድ ውስጥ የገቡ ነፃ አውጪዎች ነበሩ ነቢዩ ሙሀመድ ﷺ እና ባልደረቦቻቸው። ወደፊትም የሙስሊሙ ተግባር ይሄው ነው። ሙስሊም ነፃ ግለሰብን ባሪያ አያደርግም፤ መፅሀፍ ቅዱስ እያጣቀሰ ሰዎችን ባሪያ የሚያደርግ እስከኖረ ድረስ ግን ሙስሊሙ ባሪያውን ነፃ የማውጣት የሰው-ነት ግደታ አለበትና ገዝቶ ነፃ ያወጣል። ይህ ነው ሰብዓዊነት! ይህ ነው እኩልነት!

ከመሞት፡ ከመቅለጥ፡ ሜዳ ላይ ከመቅረት፣

በጁጉ ይሻላል ነጻነት ተስፋ አርጎ መኖር በባርነት፣

እያገለገሉ ተስፋን በልብ ይዞ በሂወት መቆየት፣

መግደሉ መስለቡ ባይቻል መማረክ፣

ከመሞት ይሻላል፡ ለተስፋ መም-ማረክ፣

ከሌላው ህዝብ አንፃር ነፃነቱ ቢያንሰው'ጫንቃ'ተባለ እንጂ፣

ባርነት አይደለም ተማርኮ የገባ ከሙስሊሞች እጂ፣

ካሳዳሪው ጋራ ...

ከሚበላው በልቶ ከሚጠጣው ጠጥቶ ከሚለብሰው መልበስ፣

አይገኝም ከቶ በባርነት ታሪክ በዓለም ላይ ቢዳሰስ፣

ሊገድለው የመጣን እንከባክቦ'ሚያኖር፣

ምድር ቢበረበር፡ ሰማይ ቢመረመር፣

ከወደት ይገኛል ከሙስሊም ደጅ በቀር፣

ያ! ማ ደጉ ነቢይ የዓለማቱ እዝነት፣

አደራን አብዝቷል ለባሪያ ነፃነት፣

ይህ ነው የኛ ኢስላም ለባሮችም አዛኝ፣

ሊገድለው የመጣን

ተንከባክቦ አኑሮ ነፃነት የሚያስገኝ፣

ጥቀስ! ታሪክ ካለህ፣

ከነቢይ፣ ከፃድቅ፣ ከቄስ ከመነኩሴህ፣

ለባሪያ ነፃነት እጅግ የሞገተ፣

'ጫንቃነት'አሳስቦት ነፃነታቸውን ተናዞ የሞተ፣

ከአድሱ ካሮአጌው ካዋልዳቱም ጥቀስ፣

አንድም ካላገኘህ

በየትኛው ሞራል አህመዴን ትወቅስ?

**ምንጭ**

ትንቢተ-ነቢዩ ሙሀመድ ከሚለው መፅሀፍ የተወሰደ፡ ገፅ 188-200